# የምሥራች

## በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## በኒው ዮርክና አካባቢው ሀገረ ስብከት ለምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሙሉ ከሁሉ አስቀድሞ

እንኳን ለ፳፻፲፫(2013) ዓመተ ምህረት የጌታን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት በሰላም   አደረሳችሁ በዓሉ የሰላም የፍቅር የአንድነት በዓል እንዲሆንላችሁ እየተመኘን በሀገረ ስብከታችን ስም ይህ የእንኳን አደርሳቸሁ መልእክት ስናስተላልፍ ለሀገራችንና ለህዝባችን ሰላምና በረከት በመመኘት ይህም በረከት በምድራችን እንዲበዛ በመጸለይ ነው

*“መልአኩም እንዲህ አላቸው፤እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” (ሉቃ 2፥10)።*

እንደ ዛሬው ሁሉ ያንጊዜም ጌታችን ሲወለድ ዓለም በጨለማው ውስጥ ነበረች። ሰዎች መሽቶ ሲነጋ ምን እንደሚሰሙ እርግጠኞች አልነበሩም። የዓለም የግፍ አገዛዝ ድሆችን አደህይቶ ላላቸው ደግሞ በዚያው ላይ ለመጨመር በሚደረገው ጥረት ያለውን ሁሉ በመሰብሰብ የሰውን ልጅ መከራ ከብረት አጠንክሮት ነበር። አሁንም እንደምናየው የሰው ልጅ ወጥቶ የመግባት ዋስትና አልነበረውም። በአንድ ቃል ሲቀመጥ የሰው ልጅ ከደስታ ጋር ተለያይቶ ነበር። የሚታየው ሁሉ ፍርሀትን መጨመር እንጅ የደስታ ጭላንጭል የሚያሳይ አልነበረም። በዚህ ዘመን ነው የደስታችን ምንጭ የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው። ስለዚህ ስለጌታ ልደት ስናነሣ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊና መለኮታዊ ዕቅድ ፍጻሜ መሆኑን በሚከተሉት ነጥቦች እንገነዘባለን። በነጥብ በነጠብ ብንጠቅሳቸው የነቢያት ትንቢትና ፍጻሜ፣ እግዚአብሔርና የዓለም ታሪክ፣ የደስታው አዋጅ የሚሉትን ነጥቦች እንመለከታለን።

### 1. *የነቢያቱ ትንቢትና ፍጻሜው፦*

በኦሪት ዘፍጥረት ትረካ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ክፉና ደጉን በራሳቸው ሥልጣን መወሰን የሚችሉ አምላኮች ለመሆን ባደረጉት ጥረት ራሳቸውን ሕይወት ከሆነው እግዚአብሔር ሲያገሉና ለሕይወት የሚኖሩ ሕያዋን መሆናቸው ቀርቶ ለመሞት የሚኖሩ ሙታን ሲሆኑ ለሕይወት የፈጠራቸው እግዚአብሔር ዳግም ወደ ሕያዋንነት እንደሚመልሳቸው የተናገረው ቃል ነበር። በዚህ ቃልም በሔዋንና እርሷን ባሳታት እባብ መካከል ጠላትነት እንደሚነሣና ከሴቲቱ የሚወለድ ልጅም የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ እንዲህ የሚል ተስፋ ሰጥቶ ነበር። *“በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ” (ዘፍ 3:15)።*

ይህ ለመጀመሪያዋ ሴት የተነገረው የተስፋ ቃልም ኋላ ላይ እግዚአብሔርን የሚያምንና የሚተማመን ሆኖ ለተገኘው ለአብርሃም “በዘርህ አሕዛብ ይባረካሉ” በሚል ቃል በድጋሜ ተነገረ። ከዚህ የተስፋ ቃል በስተቀር የሰው ልጅ አንዳችም ተስፋ አልነበረውም። የሚኖረው ለመሞት ነበር። ግራና ቀኙን፣ ክፉና ደጉን መለየት ተስኖት ክፉና ደጉን እንዲለይበት የተሰጠው የሙሴ ሕግም ኃጢአተኛነቱን እያመለከተ “በድንጋይ ተወግረህ፣ በእሳት ተቃጥለህ መሞት ይገባኻል!” ብሎ እየፈረደበት፣ በቅጡ እንኳን የማይረዳው የገዛ ምኞቱ ባርያ ሆኖ፣ በመኖርና በመሞት መካከል ይህ ነው የሚባል ልዩነት ጠፍቶ ነበር። የሚከተሉት የቅዱስ ጳውሎስ ቃላት ያኔ የነበረውን (ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በማይከብርበት ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች የሚኖሩበትን) በሞት ጥላ ሥር የሚማቅቅ የሰው ልጅ ኑሮ በሚገባ ይገልጹታል። በተለይም አሁን በሀገራችን በመግደልና

በማስገደል ያሉ ሰዎች ከሁሉ በፊት ደስታ አልባ ሆነው የሚታዩት እነርሱው ገዳዮቹ ናቸው። እንደነዚህ ያሉትን ሐዋርያው እንደሚከተለው ይገልጻቸዋል። *"እኔ ግን ከኃጢኣት በታች ልሆን የተሸጥሁ ሥጋ ነኝ፤ የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና፤ ዳሩ ግን የምወድደውን እርሱን አላደርገውም። እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ? ለዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" (ሮሜ 7፡ 15-24)*

ለዚህ የሰው ልጅ ጥያቄ እውነተኛ መልስ የሚሰጥና የሰውን ልጅ ከዕረፍተ ቢስነቱ የሚገላግል አንድም አዳኝ አልተገኘም። የሰውን ልጅ በሕይወት እንዲኖር የፈጠረው እግዚአብሔር ግን ፍጥረቱን እንዲህ ባለው ጨለማ ይተው ዘንድ አልመረጠም። ይልቁንም ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ "አይዞህ! እኔ አድንሃለሁ!" ሲል መለሰለት። ነቢያቱም በየተነሡበት ዘመን ከነበረው ራስ ወዳድነት ከወለደው መከራ፣ አልጠግብ ባይነት ከወለደው አስከፊ ማኅበራዊ ቀውስ፣ ተስፋ ማጣት ከወለደው የሞራል ዝቅጠት ሁሉ ከፍ ብለው፣ ከጨለማው በላይ የሆነውን የሚመጣውን እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ መፈጸም ይጠብቁ ነበር። ተስፋው የሚፈጸመውም ስለሰው ልጅ በምትቀናው የእግዚአብሔር ፍቅር እንጂ በሰው ልጅ ቅድስና ብቃት እንዳልሆነ ነቢያት "የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል" (ኢሳ 9:7) እያሉ በጉጉት ይናገሩ ነበር።

ጊዜው ሲደርስም የሰዎችን ድካም ስለእነርሱ ተሸክሞ የሰው ልጆችን የእግዚአብሔር ልጆች ያደርግ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ። ሕጻን ተወለደልን፤ ወንድ ልጅም ተሰጠን፤ ድካማችንን የሚረዳልን ሊቀ ካህናት፣ መከራችንን የሚቀበልልን ቤዛ አገኘን። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ ብሎ እንደጻፈ፡- *"የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም። ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው። እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።"* (ዕብ 2፡ 16)

ነቢዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ቅንዓት የሰጠችንን ተስፋ እንዲህ ይገልጸዋል።

> *"ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።" (ኢሳ 9፡ 6-7)*

ተስፋችን የአብርሃም ዘር የሆነው ይህ ሕጻን ነው። ወንድ ልጅ ነው፤ አለቅነት በጫንቃው ላይ ነው። ምክሩ ለሚሰማው ድንቅና ሕይወት የሚገኝበት፣ ኃያልነቱ ድካም የማያገኘው አምላካዊ፣ አባትነቱ ለዘለዓለም የሚያስተማምን፣ ለሚተማመኑበትም ሰላማቸው የሚሆናቸው አለቃ ነው።

ከአንዲት ከተመረጠች ድንግል በድንግልና ይወለዳል። በገዛ ኃጢኣተኝነቱ የተነሣ ከእግዚአብሔር ተጣልቶ ሕይወት ርቆት የሚኖረው ለመሞት ሆኖበት የነበረውን የሰው ልጅን ከእግዚአብሔር ያስታርቃልና እናቱ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ በማለት "አማኑኤል" ትለዋለች። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ። *"ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" (ኢሳ 7፡14)*።

ዘመኑ ሲደርስ እግዚአብሔር ሥራውን በእርሷ ላይ እንዲያከናውን "እሺ" ብላ በፍጹም እምነት የምትታዘዝ፣ በሴትነቷ ሔዋንን በአማኝነቷ አብርሃምን የምትመስል ድንግል ተገኘች። እግዚአብሔርም የዘለዓለም ዕቅዱን በእርሷ ለመሥራት ፈቃደኝነቷን ሊጠይቅ መልአኩን ላከ። እርሷም ለእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራ ራሷን አሳልፋ በመስጠት "እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደቃልህ ይደረግልኝ" አለች። መላ ሕይወቷንም እግዚአብሔር በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊያከናውነው ላቀደው የሕይወት ዕቅድ በእሺታ አቀረበች (ሉቃ 1፡27-38)።

2. **<u>እግዚአብሔርና የዓለም ታሪክ፦</u>**

በክርስቶስ ልደት ከተከናወኑት ክንውኖች አንዱ እግዚአብሔር በዓለም ታሪክ ላይ ያለው የበላይነት ነው፡፡ እውነት ነው በኃጢአት የተያዘው ዓለም ጉልበተኛ ቄሣሮች የሚዘውሩት፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ በራስ ወዳድነትና በፍርኀት የታሠረበት፣ ሁሉም "አለችኝ" በሚላት ስፍራው ላይ አምላክ ለመሆን በሚያካኺደው ጦርነት የተቃወሰ ነው።በመሞትና በመግደል ጨለማ የተዋጠ ነው። የሚጻፈውም አለማመን በወለደው ፍርኀት፣ ፍርኀት በወለደው ጥርጣሬ፣ ጥርጣሬውም ባሳደገው የጥላቻ ጥላሸት የሚጻፍ ታሪክ ነው።

ነገር ግን ስለሰው ልጅ የሚቀናው የእግዚአብሔር ቅናት የሰው ልጅን ሕይወት እንጂ ሞት የማይወድደው ጌታ በዚህ ጨለማ ውስጥም የሚተባበሩትን ሰዎች እየፈለገ ከእነርሱ ጋር ለብዙዎች ብርሃንን ያወጣ ዘንድ ይሠራል። የክፉዎችን ክፋት ለበጎ ዓላማው ይጠቀምበታል። ከሥጋዊ ሰዎች ከንቱነትም ለሚወድዱት ሰዎች በረከትን ያበቅላል። እርሱን የሚተማመኑት ሰዎችና ሰይጣን በሠሩት ጨለማ ውስጥ የእግዚአብሔርን ብርሃን ያያሉ፤ በረከቱን ያገኛሉ። እርሱን የማይተማመኑት ጸጋው ያመልጣቸዋል፤ዐይኖቻቸው በገዛ ጨለማቸው ታውረዋልና። በልደቱ ታሪክ የምናየው ይህንን ነው። አንዳንዶች በፈቃዳቸው ብዙዎች ግን ያለፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር ዓላማ ይሠራሉ። "ፈቃድህ በሰማያት እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን!" በማለት ፈቃዳቸውን ለእርሱ ፈቃድ አሳልፈው ሰጥተው ከእርሱ ጋር የሚሠሩ ብቻ ግን ይጠቀማሉ።

አውግስጦስ ቄሣር በግዛቱ ያሉትን ሰዎች ብዛት ቆጥሮ ሰፍሮ ሥልጣኑን ለማረጋጋት የሕዝብ ቆጠራ ዐወጀ። እግዚአብሔር ግን የቄሣርን ከንቱነት እውነተኛው የሰላም አለቃ መሲሑ ሕጻን ትንቢት በተነገረላት ቦታ በቤተ ልሔም የሚወለድበት ምክንያት አደረገው፤ ሚክያስ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበርና። *አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል። ስለዚህ ወላጂቱ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፤የቀሩትም ወንድሞቹ ወደ እስራኤል ልጆች ይመለሳሉ። እርሱም ይቆማል፥በእግዚአብሔርም ኃይል በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ግርማ መንጋውን ይጠብቃል፤ እነርሱም ይኖራሉ፤እርሱ አሁን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናልና። (ሚክ 5፡2)*

ሉቃስ ይህንን ነገር እንዴት እንደተከናወነ በሚያስገርም የአተራረክ ስልት እንደሚከተለው ይተርክልናል።

> *"በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች። ቄሬኔዎስ በሶርያ አገር ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆነ። ሁሉም እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ። ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም*

*ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ።" (ሉቃ 2፡1-5)*

የእግዚአብሔር ሥራ አስፈጻሚ የሆነው አውግስጦስ ቄሣር የእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ሲደርስ ሰዓቱን ጠብቆ ዐዋጁን አወጣ፤ ወደፊትም ወደኋላም ማለት የለም። ጊዜ የእግዚአብሔር ነው፤እናም ይሠራበታል።በዚያ ሰዓት ድንግል መዉለጃዋ ደረሰ። ለአንዲት ነፍሰ ጡር ከ180 ኪሎ ሜትር በላይ የሆነ አባራማ መንገድ ለቀናት መጓዝ ምን ያኽል አድካሚ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። የቄሣር ትእዛዝ ነውና መጓዝ ግድ ነበር። በዚያ ሲደርሱ የጠበቃቸው የእንግዶች ማረፊያ ቦታ እንኳን አልነበረም፤ የተገኘው በረት ነበር። ሉቃስ ትረካውን ይቀጥላል፡-

*"በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፥ የበኵር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ።" (ሉቃ 2፡ 8)*

መሲሑን ይጠብቁ የነበሩ ብዙ ነበሩ። መሲሑ ሲመጣ ግን ለመቀበል በቦታው አልተገኙም። እግዚአብሔርን እነርሱ በሚጠብቁት መንገድ ብቻ ይሠራል ብለው አስበዋልና የእግዚአብሔርን ያልተጠበቀ አሠራር ማስተናገድ የሚችል አእምሯዊ ዝግጁነቱ አልነበራቸውም። እግዚአብሔርን በፍቅርና ሕይወት ሰጪ ሥራው ውስጥ አስተውሎ ከመፈለግ ይልቅ በሰው ሥርዓትና አስተሳሰብ እንዲሠራ መጠበቅ እንዲህ እርሱ ሲመጣ እንዳናገኘው ያደርገናል።

## 3) የደስታው አዋጅ፡-

### 3.1) የሰማይና የምድር ዕርቅ አዋጅ፡-

የሕጻኑ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድና የእግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆን ሰማይና ምድርን አገናኘ። የማይታየው ኃያሉ አምላክ ለሰው ልጅ ሕይወት ይሆን ዘንድ ሰው ሆኖ ውሱን ሕጻን ሆኖ ተወልዶ፣ በከብቶች መመገቢያ ግርግም ተኝቶ፣ የአንዲት ታናሽ ብላቴና ጡት ሲጠባ ቢያዩት ሰማያውያን መላእክት እንደወትሮው ተሠውረው መቆየት አልሆነላቸውም፤ በሜዳ ለነበሩ ምድራውያን የበግ እረኞች ተገልጠው ታዩ። እናቱ በጨርቅ የጠቀለለችው ታናሹ ሕጻን የሰው ልጅ ለዘመናት የታሠረበትን የፍርኀት መጋረጃ በኃይሉ ተርትሮ ጣለው። መላእክቱ ሲገለጡላቸው እረኞቹ መፍራታቸው የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ምን ያክል በፍርኀት ታሥሮ ይኖር እንደነበር ያሳያል። በእግዚአብሔር እንደሚወደድ ያልገባውና በእግዚአብሔር ፍቅር ያላረፈ ሰው በፍርኀት ታሥሮ ይኖራል። ከመልአኩ የተገኘው ቃል ግን እጅግ የሚያጽናና ነበር። እርሱም፡-

*"እነሆም፥ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፥ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ። መልአኩም እንዲህ አላቸው። እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።" (ሉቃ 2፡ 9-11)*

ይህ ቃል የዓለም ደስታ ነበር። እውነትም ታላቅ ደስታ ታላቅም የምሥራች ነው። አምላክ ሰው ሆነ። የሰው ምስክርነት "በሁለት ምስክሮች ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ይጸናል"(ዘዳ. 19:15)። ይህ የመልአኩ ቃል ግን በእልፍ አእላፍ መላእክት መገኘት እውነትነቱ ተመሰከረ።

*"ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችሁ። ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፦ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።" (ሉቃ 2:12-14)*

አዎን! ቅዱስ ጳውሎስ "እርሱ ሰላማችን ነውና" (ኤፌ 2:14) ብሎ እንደተናገረው የልባችን ሰላም የነፍሳችንም ዕረፍት ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በከብቶች በረት በግርግም ውስጥ ተገኘልን። እውነት ነው በምድር ሰላም ሆኗል። ፈቃድህ በሰማያት እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን የሚሉ ፈቃዳቸውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ላደረጉ ሁሉ ይህ የማይናወጥ የልብ ሰላም ተሰጥቷል። ይህ ሰላም እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ እንዲሁ በነጻ የሰጠውን ዕርቅ በመቀበል የሚገኝ ሰላም ነው። ይህ ዕረፍት ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን የሚገኝ ዕረፍት ነው።

### 3.2) የደስታ አዋጅ፦

እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሆነ። በመካከል መለየት የሌለበት መገኘት ነበር። አምላክ ሰው ሆነ፤ ሰው አምላክ ሆነ። ጌታ የተወለደበት ቦታ በረት ነበር። መላእክት ግን እረኞቹ ደስታችሁ የሚገኘው በዚህ በረት ነው ሲሉ ወደ በረት መሯቸው፤ደስ ይበላችሁ! ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር በመገኘት እንጂ እዚህ ቦታ ወይም እዚያ ቦታ በመገኘት ወይም ደግሞ ሀገር ለሀገር በመዞር የሚገኝ አይደለምና። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ምን ይጎድልብናልና እንዘን? ክርስቶስ ሰላማችን ነው። ክርስቶስ ደስታችን ነው፤ አሜን።

### 3.3) ከኃጢአት የመዳን አዋጅ፦

ቅዱስ ሉቃስ ሲተርክልን በመጀመሪያ መልአኩ ገብርኤል ድንግል ማርያምን ሲያበሥራት የምትወልደውን ልጅ ***ኢየሱስ*** ብላ እንደምትሰይመው ነግሯት ነበር። የዚህን ስም ትርጉም ሌላኛው ወንጌላዊ ማቴዎስ እንዲህ ያቀርበዋል። "እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ" (ማቴ 1:20)።

ይህ ሕጻን ንጹሕ ሕጻን ብቻ አይደለም፤ የቆሸሹትንም ንጹሕ የሚያደርግ ነው እንጂ። ይህ ሕጻን ኃጢአት የሌለበት ሕጻን ብቻ አይደለም፤ በኃጢአት እሥራት የሚኖሩትን ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያድንና ኃጢአታቸው ካመጣባቸው የፍርኀት እሥር ነጻ የሚያወጣና ደስታና ሰላም ከሌለው የሞት ኑሮ የሚታደግ አዳኝ ሕጻን ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ "የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ታደርጋለች" እንዳለው ይህ ሕጻን የተሰጠን፣ ስለጸሎታችን ብቃት፣ ስለ ጽድቃችን ከፍታ አይደለም። እንዲሁ እግዚአብሔር ስለወደደንና ስለቀናልን እንጂ።

***መደምደሚያ***

**ድርሻችን ምን ይሁ?**

ቅዱስ ሉቃስ ጥሩ አድርጎ አቅርቦታል። እንደ እረኞቹ መጀመሪያ ፍርኀትና ጥርጣሬን ጥሎ ማመን ነው። ከዚያ ሕጻኑን ፈልጎ ማግኘት ነው። እግዚአብሔር የሰጠውን ፍቅር በትሕትና መቀበል ነው። በኃጢአታችንንና በበደላችን ሙታን ሳለን ያልተወን ይልቁንም አንድ ልጁን የሰጠንን አብን፣ ሰው የሆነልን ወልድን፣ በመንፈስ ቅዱስ ደስ እየተሰኙ ማመስገን ነው።

> *“መላእክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ፥ እረኞቹ እርስ በርሳቸው። እንግዲህ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ። ፈጥነውም መጡ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ። አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገለጡ። የሰሙትም ሁሉ እረኞቹ በነገሩአቸው ነገር አደነቁ።” (ሉቃ 2፡ 15-17)*

እኛስ ለዚህ ለተሰጠን ከአእምሮ በላይ ለሆነ ስጦታ ከምስጋና ሌላ ምን ልንሰጥ እንችላለን? እርሱ ይህን ያህል እኛን ከወደደን እኛም ሕይወታችንን ሁሉ ለዚህ ፍቅር ምላሽ መስጠት ልናደርገው ይገባናል። ይህ ፍቅር የማይታይበት አንዳችም የሕይወታችን ማይክሮ ሰከንድ ሊኖር አይገባም። ይህን ፍጹም ፍቅር ገፍተን የት ልንደርስ ነው?

እረኞች ያኔ ያገኙት በበረት ነው። ያኔ የዓለሙ ፈጣሪ ለዓይን በሚከፋ፣ ለአፍንጫ በሚከረፋ በረት ይወለዳል ብሎ ያሰበ አልነበረም። በበረት የሚወለድ ጌታ ለዓለም እንግዳ ነገር ነው፤ አእምሮዋም ሊረዳው ያዳግተዋል፡፡

ዛሬም ኢአማንያን በዓለም ላይ የሚያዩት ክፋትና እብደት በዓለም ውስጥ ሕይወትን የሚሠራውን እግዚአብሔርን እንዳያዩት ጋርዶባቸዋል። ስለዚህም ጮኽ ብለው “እግዚአብሔር የለም!” ይላሉ፡፡ በስም ክርስቲያን ነን የምንል ብዙዎችም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አጠገባችን ባለው ወንድማችን/ እኅታችን ውስጥ ማየት ተስኖናል። ወንድማችንን/ እኅታችንን ስንመለከት እኛ የምናየው የወንድማችን የእኅታችን ድካም፣ ስንፍና፣ ጉስቁልና ወይም ደግሞ ሀብት፣ ንብረት፣ ውበት፣ ዕውቀት ነው፤ በዚህም የተነሣ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ ፍቅር የተራበች ነፍሱን፣ እግዚአብሔርን የተጠማች መንፈሱን፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በዚያ ሥጋዊ ወይም መንፈሳዊ ረኀብ በኩል ያንን ሰው ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ወራሽነት ለማድረስ የሚሠራውን እግዚአብሔርን ማየት ይሳነናል። ስለዚህም ወንድማችንን ከማገዝ ይልቅ በስሕተቱ ወይም በክፋቱ ልንፈርድበት እንቸኩላለን። እግዚአብሔር ለእኛ ምን ያህል ይቅርታ እንዳደረገልን ስለማናስተውልም ወንድማችንን ይቅር ማለት ተስኖን ሰላም ርቆን እንታያለን፡፡ በተለይም በአሁኑ ስአት በሀገራችን የሚታየው ከራስ ወዳድነት የተነሳ ጦርነት ከምኑም የሌሉበትን ንጹሐንን በመግደል ደስታ ለማግኘት የሚጥሩ ሁሉ መርዶ እንንገራቸሁ! ሰው ገሎ ውሸት ዋሽቶ ሰላም የለም። ሰላም ከሌለ ደግሞ ደስታ የለም። የምናደርገው ነገር ሁሉ ደስታችን የሚሰርቅ እንጅ ደስታ የሚለግስ አይደለምና ወደ ደስታችን ለመመለስ ከክፋትና ከክፉ አድራጊዎች እንጠበቅ። በተለይም ይህን ለሰው ልጅ ክብር ከእግዚአብሔር የተሰጠን የልደት ቀን ስናክብር ልባችን ወደ ሰላም እንመልስ።

ሕጻኑን በበረት ውስጥ ማግኘት የማይችሉ ሕጻኑን ስላላገኙት ሰላም የላቸውም፤ ደስታን በማጣትም ይቅበዘበዛሉ። ደስታው፣ የምሥራቹና ለሰው ሁሉ የሚሆነው ታላቁ ዜና ሕጻኑ ነውና። ጠብ ባለበት የፍቅርን ጭላንጭል የሚያቀጣጥሉ፣ የሞት ጥላ ባጠላበት የእግዚአብሔርን ብርሃን ይዘው የሚገኙ ሰዎች ግን ሕጻኑን ኢየሱስ ክርስቶስን በበረት ያገኙትንና ደስታ የበዛላቸው እረኞችን ይመስላሉ፤ በማይጠበቅ ቦታ ውስጥ የተወለደውን ሕጻን አግኝተውታልና።

እንግዲህ ተስፋ ተሰጥቶን የነበረው የጠላታችንን ራስ የሚቀጠቅጥልን ሕጻን መጥቶልናልና ደስ ይበለን! ደስታ ያሳጣንን፣ ሰላም የነፈገንን ጠላታችንን ኃጢአትን እንዲቀጠቅጥልንም ወደ ሕይወታችን በንስሐ እንጋብዘው። በፍቅርና በይቅርታ መንፈስ ሆነን ቅዳሴ በቀደስን ቁጥር ስጋውንና ደሙን በመስጠት "ብሉኝ፤ ጠጡኝ፤ ወደ ሕይወታችሁ አስገቡኝ" እያለ እየመጣ ነውና ደስ ብሎን እንቀበለው። ድንግል በልጇ መዓዛ ደስ ይላት እንደነበር በጣፋጭ መዓዛው ደስ ይበለን። በተለይም ዛሬ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ የሞት ጥላ በአጠላበት ለምን እኛ እንጋደል? በመግደል መች ደስታ ተገኘ? ስለሆነም አሁን ወደ እውነተኛው ነገር እንመለስ። ይህን የልደት በዓል ለሰው በመቆም እንጅ ሰው በመግደል አንቀበለው! የሰላም አምላክ ከሁላችን ጋር ይሁን።

በአርያም ለእግዚአብሔር ምሥጋና፤ በምድርም ሰላም፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን!

አሜን!

እግዚአብሔር አገራችን ኢትዮጵያን ይባርክ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ይጠብቅ።

**አባ ጴጥሮስ**
በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የኒው ዮርክ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት
ሊቀ ጳጳስ